# ኢትዮ-ቻምበር

## ዜና መጽሔት

በኢትዮጵያ ንግድና የዘርፍ ማኅበራት ምክር ቤት የመረጃና አቅም ግንባታ ዳይሬክቶሬት በየወሩ የሚዘጋጅ የዜና መጽሄት (ነሃሴ የመጀመሪያ ግማሽ ወር 2011 ዓ.ም.)

# ም/ቤቱ የንግድ ደን እና እንጨት ማቀነባበሪያ ኢንዱስትሪዎች ልማት ችግሮች እንዳሉበት በጥናት ደርሼበታለሁ አለ




ከግራ ወደ ቀኝ፡- መልአኩ እዘዘው (ኢንጂነር) የኢትዮጵያ ንግድና የዘርፍ ማኅበራት ምክር ቤት ፕሬዚደንት እና

ግርማ አመንቴ (ዶ/ር) በምክትል ፕሬዚደንት ማዕረግ የኦሮሚያ ገጠር ልማት ክለስተር ኃላፊ

**በኦሮሚያ ክልል የንግድ ደን እና እንጨት ማቀነባበሪያ ኢንዱስትሪዎች ልማት ላይ ችግሮች መኖራቸውን የኢትዮጵያ ንግድና የዘርፍ ማኅበራት ምክር ቤት ያስጠናው ጥናት አመላከተ፡፡**

**(የዚህን ዘገባ ሙሉ መረጃ ገጽ 2 ላይ ይመልከቱ)**

## በክልሉ የንግድ ደን . . . (ከገጽ 1 የዞረ)



አቶ ታደሰ ገና የኦሮሚያ ንግድና የዘርፍ ማኅበራት ምክር ቤት ፕሬዚደንት

ጥናቱ የቀረበው የኢትዮጵያ ንግድ እና የዘርፍ ማኅበራት ምክር ቤት ከኦሮሚያ ንግድና የዘርፍ ማኅበራት ምክር ቤት ጋር በመተባበር ነሀሴ 2 ቀን 2011 ዓ.ም. በኢሊሊ ኢንተርናሽናል ሆቴል ባዘጋጀው የመንግሥትና የግሉን ዘርፍ የምክክር መድረክ ላይ ነበር፡፡

የመድረኩ ዓላማ በኦሮሚያ ክልል የንግድ ደን እና የእንጨት ማቀነባበሪያ ኢንዱስትሪዎች ልማት ላይ ያሉ ችግሮችን አስመልክቶ በምክር ቤቱ የተጠናው ጥናት ላይ በመምከር የግሉን ዘርፍ አቋም ለማንጸባረቅ ነው፡፡

የሀገራዊ ምክር ቤቱ ፕሬዚደንት መልአኩ እዘዘው (ኢንጂነር) ባደረጉት ንግግር ቀደም ሲል ምክር ቤቱ በኢትዮጵያ የንግድ ደን ልማት እና እንጨት ማቀነባበሪያ ኢንዱስትሪዎች ልማት ችግሮቻቸውና መፍትሄዎቻቸው ላይ ጥናት አስጠንቶ በሀገር አቀፍ ደረጃ የመንግስትና የግሉ ዘርፍ ምክክር መካሄዱን አስታውሰው በዘርፉ የበለጠ ፋይዳ ያለው ለውጥ ለማምጣት በክልል ደረጃም መካሄድ ስላለበት ይህ ጥናት መደረጉን ገልጸዋል፡፡

የኦሮሚያ ንግድና የዘርፍ ማኅበራት ምክር ቤት ፕሬዚደንት አቶ ታደሰ ገና በበኩላቸው ጥናቱ የኦሮሚያ ደን እንዴት ችግር ላይ እንደወደቀና የግሉ ዘርፍ በንግድ ደን ውስጥ እንዲሰማራ አመላካች ዝርዝር ሀሳቦችን መያዙን ገልጸው የኦሮሚያ ገጠር ልማት ቢሮን ጨምሮ ጉዳዩ መስመር እንዲይዝና ጥናቱ እንዲሳካ ላደረጉ አካላት በሙሉ ምስጋናቸውን ለግሰዋል፡፡

በዕለቱ የመክፈቻ ንግግር ያደረጉት በምክትል ፕሬዚደንት ማዕረግ የኦሮሚያ ገጠር ልማት ክለስተር ኃላፊ ግርማ አመንቴ (ዶር.) በሀገሪቱ የገበያ ፍላጎት ችግር ሳይኖር ነገር ግን ከፍተኛ የሆነ የፍላጎትና የአቅርቦት ክፍተት መኖሩን አውስተው የደን ሽፋናችንን ለማሳደግ በደን ልማት ላይ ያለንን ባህል በመለወጥ ይበልጥ አሳታፊ ማድረግ እንደሚገባን አሳስበዋል፡፡

የጥናት ሰነዱ የፖሊሲና መመሪያዎች፣ የፋይናንስ እንዲሁም የቅንጅታዊ አሠራር ችግሮችን ጨምሮ ሌሎች በርካታ ችግሮችን በመለየት የመፍትሄ ሀሳብ አመላካች ዝርዝር ነጥቦችን ያመላከተ ሲሆን ጉዳዩ የሚመለከታቸው የመንግሥት ተወካዮች፣ የጂማ ደን አልሚዎች፣ የአጋሮ ከተማ የእንጨት ውጤቶች አምራቾች፣ የጂማ እና የአዲስ አበባ ንግድ ምክር ቤት ተወካዮች እንዲሁም የዓለም ባንክና የዩኤንዲፒ ተወካዮች በተገኙበት ለውይይት ቀርቧል፡፡

በመጨረሻም በመድረኩ ላይ የተሰጡ አስተያየቶችን በማካተት የግሉን ዘርፍ አቋም የሚያንጸባርቀው ሰነድ በይፋ ከጸደቀ በኋላ ጉዳዩን በባለቤትነት በመከታተል የሚያስፈጽም ከተለያዩ የፌዴራልና የክልል ቢሮዎችና ከግሉ ዘርፍ የተውጣጣ ግብረ ኃይል ተቋቁሟል፡፡

መድረኩ የተዘጋጀው ከዓለም ባንክ በተገኘ የገንዘብ ድጋፍ እንደሆነም ታውቋል፡፡



የምክክር መድረኩ ከፊል ገጽታ

**‹‹በሀገሪቱ የገበያ ፍላጎት ችግር ሳይኖር የፍላጎትና የአቅርቦት ክፍተት በመኖሩ የደን ሽፋናችንን ለማሳደግ በደን ልማት ላይ ያለንን ባህል በመለወጥ ይበልጥ አሳታፊ ማድረግ ይገባናል››**

ግርማ አመንቴ (ዶር.)

በምክትል ፕሬዚደንት ማዕረግ የኦሮሚያ ገጠር ልማት ክለስተር ኃላፊ

# የደን ልማት የዘርፍ ማኅበራትን ማቋቋም እንደሚያስፈልግ ተጠቆመ

የኢትዮጵያ ንግድና የዘርፍ ማኅበራት ምክር ቤት የኦሮሚያ የንግድ ደን እና የእንጨት ማቀነባበሪያ ችግሮች እና መፍትሄዎችን አስመልክቶ ባስጠናው ጥናት ላይ የደን ልማት የዘርፍ ማኅበራትን ማቋቋም እንደሚያስፈልግ አመላከተ፡፡

ምክር ቤቱ ከኦሮሚያ ንግድና የዘርፍ ማኅበራት ምክር ቤት ጋር በመተባበር ነሃሴ 2 ቀን 2011 ዓ.ም. በኢሊሊ ሆቴል ባዘጋጀው የመንግስትና የግሉ ዘርፍ የምክክር መድረክ ላይ የጥናት ሰነዱን የመንግሥት ተወካዮች፣ በደን ልማትና እንጨት ማቀነባበሪያ የተሰማሩ የግሉ ዘርፍ ተወካዮች፣ የምክር ቤት ተወካዮችና የልማት አጋሮች በተገኙበት ለውይይት አቅርቧል፡፡

ጥናቱ በዋናነት ስድስት ያህል ችግሮች በዘርፉ ላይ እንደሚታዩ የለየ ሲሆን የመፍትሄ ሀሳብ አመላካች ዝርዝር ጉዳዮችንም አካቶ የያዘ ነው፡፡

እንደ ጥናቱ ከሆነ የመሬት ፖሊሲና መመሪያዎች የግሉን ዘርፍ በደን ልማት ላይ ከማሳተፍ አንጻር ግልጽ አለመሆን፣ የፋይናንስ አቅርቦት ችግር፣ የመንግሥትና የግሉ ዘርፍ የትብብር መድረክ አለመኖር፣ በደን ልማት ዙሪያ በቂ ጥናት አለመኖሩ፣ የምርት አቅርቦትና የገበያ ችግር፣ የሚሉት እንደ ችግር የተለዩ ሲሆን የደን ልማት የዘርፍ ማኅበራት



መልአኩ እዘዘው (ኢንጂነር) የም/ቤቱ ፕሬዚደንት

አለመቋቋምም የችግሩ አካል ሆኖ ቀርቧል፡፡

ጥናቱ ላይ እንደተመለከተው በሥራ ላይ ያለው መመሪያ ለግሉ ዘርፍ የደን ተጠቃሚነት ዋስትና እንደማይሰጥ በመግለጽ የደን ኢንተርፕራይዞች እንዲቋቋሙ



ግርማ አመንቴ (ዶ/ር) በም/ፕሬዚደንት ማዕረግ የኦሮሚያ ገጠር ልማት ክለስተር ኃላፊ

በማድረግ የንግድ ደን እንዲያለሙ እውቅና መስጠት እንደሚያስፈልግ በመፍትሄነት ያስቀምጣል፡፡ የመሬት ፖሊሲዎችን በማሻሻልም ለባለሀብቱ የረጅም ጊዜ የመጠቀም መብትን የሚያጎናጽፍ ዋስትና ሊሰጥ እንደሚገባም ይጠቁማል፡፡

የፋይናንስ አቅርቦት ችግርን አስመልክቶ የኢትዮጵያ ልማት ባንክም ሆነ ሌሎች ባንኮች ለደን አልሚው ራሱን የቻለ የደን ልማት መስኮት በማመቻቸት የረጅም ጊዜ የብድር አቅርቦት ማመቻቸት እንደሚያስፈልግም ያመላክታል፡፡

የደን ልማትን አስመልክቶ የመንግሥትና የግሉ ዘርፍ የትብብር መድረክ አለመኖሩን የሚገልጸው ጥናቱ ለዚህ በምክንያትነት ደን አልሚዎች በተደራጀ መልኩ አለመንቀሳቀሳቸው እንደሆነ ጠቅሶ የደን ልማት የዘርፍ ማኅበራትን ማቋቋም ችግሩን በዘላቂነት ይፈታል በሚል በመፍትሄነት ያስቀምጣል፡፡

የማኅበራቱ መቋቋም አልሚዎቹ በችግሮቻቸውና በጋራ ፍላጎቶቻቸው ዙሪያ በቅርበት ለመነጋገርና ድምጻቸውን በጋራ ለማሰማት እንደሚያስችልም ጥናቱ ያስገነዝባል፡፡

በዕለቱ የእንኳን ደህና መጣችሁ ንግግር ያደረጉት የኢትዮጵያ ንግድና የዘርፍ ማህበራት ም/ቤት ፕሬዚደንት መልአኩ እዘዘው (ኢንጂነር) ምክር ቤቱ በአዋጅ ከተሰጠው ሥልጣንና ኃላፊነት አንዱ የሃገሪቱን የግል ዘርፍ በመወከል የዘርፉን መብትና ጥቅም ከማስጠበቅ አንፃር በአባላቱና በመንግስት መካከል እንደ አገናኝ ድልድይ በመሆን የሚያጋጥሙ የፖሊሲ፣ የሕግ እና የአፈፃፀም ችግሮችን ለመፍታት የሚያስችሉ የምክክር ሥራዎችን መስራት ነው ብለዋል፡፡

የግሉ ዘርፍ በደን ልማት እና የእንጨት ማቀነባበሪያ ኢንዱስትሪ ዘርፍ ላይ ያለው ተሳትፎ ከፖሊሲ፣ ከህጎችና ከአሰራር ስርዓቶች በሚመነጩ ችግሮች ሳቢያ በአነስተኛ ደረጃ ላይ በመገኘቱ ችግሮቹን በመለየትና አስፈላጊውን የመፍትሄ እርምጃ በመውሰድ በዘርፉ ያለውን ተሳትፎ ማጠናከርና ማሳደግ ወሳኝ እንደሆነም አስገንዝበዋል፡፡

ከዚህ አንፃር ጥናቱ መንግሥት የግሉ ዘርፍ ከዘርፉ ተጠቃሚ የሚሆንበትን አሠራር በመፈተሽ የዘርፉን ቀጣይ ተሳትፎ የሚያረጋግጥ ህግና ሥርዓትም የሚያወጣበትን አቅጣጫ ያመላክታል የሚል እምነት እንዳላቸውም አመልክተዋል፡፡

በኢትዮጵያ የደን ልማት በስምንት ዓመት ውስጥ የሚደርስ በመሆኑ እንደ ሀገርም ሆነ እንደ ክልል ከዘርፉ በእጅጉ ተጠቃሚ መሆን ይቻላል ያሉት ደግሞ የዕለቱ የክብር እንግዳ በምክትል ፕሬዚደንት ማዕረግ የኦሮሚያ ገጠር ልማት ክለስተር ኃላፊ ግርማ አመንቴ (ዶ/ር) ናቸው፡፡

እንደሳቸው ገለጻ ከዘርፉ ይበልጥ ተጠቃሚ ለመሆን የደን ልማት ባህላችንን በመለወጥ የግሉን ዘርፍ አሳታፊ ያደረገ አሠራር ሊኖር ይገባል፡፡ ይህ ሁሉ ሲሆን ግን ሦስት መሠረታዊ ጉዳዮች መሟላት አለባቸው የሚሉት ኃላፊው ያለውን የፍላጎትና አቅርቦት አለመጣጣም ማጥበብ፣ የፋይናንስ ችግሮችን መቅረፍና በቴክኖሎጂ በመታገዝ እንደ እህልና ጥራጥሬ ምርቶች ሁሉ የንግድ ደን ምርጥ ዘርን መጠቀም ያስፈልጋል ካሉ በኋላ ጉዳዩ የራሴ ነው የሚል የተደራጀ አካል ያስፈልጋል ሲሉ የደን ልማት የዘርፍ ማኅበራት የማቋቋም አስፈላጊነትን ጠቁመዋል፡፡



የምክክር መድረኩ ከፊል ገጽታ

# ፎረሙ የሁለቱን ሀገሮች ግንኙነት ይበልጥ እንደሚያጠናክር ተገለጸ



አምባሳደር ደዋኖ ከዲር

የኢትዮጵያ ንግድና የዘርፍ ማኅበራት ምክር ቤት ከኢትዮጵያ የውጭ ጉዳዮች ሚኒስቴር እና ከኢንዶ-አፍሪካ ንግድና ኢንዱስትሪ ምክር ቤት ጋር በመተባበር ኢትዮ-ህንድ ቢዝነስ ፎረም ነሃሴ 6 ቀን 2011 ዓ.ም. በሂልተን አዲስ አበባ ሆቴል አዘጋጀ፡፡

በኢትዮጵያ የውጭ ጉዳዮች ሚኒስቴር የኢኮኖሚክ ዲፕሎማሲ ቋሚ ጸሐፊ አምባሳደር ደዋኖ ከዲር በመክፈቻ ንግግራቸው እንደተናገሩት ፎረሙ እያደገ ያለውን የሀገራቱን የቢዝነስ ግንኙነት ይበልጥ የሚያሳድግና የሁለቱ ሀገራት የንግዱ ማኅበረሰብ ግንኙነትም ይበልጥ እንዲቀራረብ የሚያስችል ነው፡፡

ከኢትዮጵያ የኢኮኖሚ ሽግግር አጀንዳዎች አኳያም ቢሆን እንደ ህንድ ካሉ ወዳጅ ሀገራት ጋር ያለንን ግንኙነት ይበልጥ ለማጠናከር በቁርጠኝነት እየሰራን ነው ሲሉም አምባሳደሩ ገልጸዋል፡፡

የምክር ቤቱ ዋና ጸሐፊ አቶ እንዳልካቸው ስሜ በበኩላቸው ፎረሙ በህንድና በኢትዮጵያ መካከል ያለውን የንግድና የኢንቨስትመንት ግንኙነት ወደ ላቀ ደረጃ ለማሸጋገር የሚያስችል ነው ብለዋል፡፡ ዋና ጸሐፊው አያይዘውም ፎረሙ የሁለቱን ሀገራት የንግድ ማኅበረሰብ



አቶ እንዳልካቸው ስሜ




ወ/ሮ ሱናንዳ ራጀንድራን

የንግድ ግንኙነታቸውን ለማጠናከርና በጋራ ለመሥራት ያላቸውን ፍላጎት ለማሳደግ መልካም ዕድል ነው ሲሉ ተናግረዋል፡፡

**ወደ ገጽ 5 ዞሯል)**

# የም/ቤቱ ፕሬዚደንት ከሁለት ምሁራን ጋር ውይይት አደረጉ

የኢትዮጵያ የንግድ እና የዘርፍ ማኅበራት ምክር ቤት ፕሬዚደንት ኢንጂነር መላኩ እዘዘው ከምክር ቤቱ ም/ዋና ፀኃፊ አቶ ውቢ መንግስቱ ጋር በመሆን ዶ/ር ጥላሁን እና አቶ መድህንን ነሀሴ 2 ቀን 2011 ዓ.ም በፅ/ቤታቸው ተቀብለው አነጋገሩ፡፡

ወደ ምክር ቤቱ የመጡበትን ዓላማ ሲገልጹ ይዘውት በመጡት አዲስ ሀሳብ በሙያቸው አገራቸውን ለማገልገል እና የዜግነት ድርሻቸውን ለመወጣት እንደሆነ የተናገሩት ዶ/ር ጥላሁን ኢትዮጵያን ምርጥ የአየር ንብረትና ዘላቂ እድገት እንዲኖራት በማድረግ እ.ኢ.አ በ2030 አለም ከደረሰችበት ፊተኛ ተርታ ለማሰለፍ የግሉ ዘርፍ ተሳትፎ ከፍተኛ እንዲሆን በማሰብ ነው፡፡ የኢትዮጵያን ችግር



ለመፍታት መንግስት መንግስታዊ ካልሆኑ በተለይም ከንግዱ ማህበረሰብ ጋር በቅርበትና በጥምረት መስራት እንደሚገባውም አክለው ተናግረዋል፡፡

በኢትዮጵያ የድህነት ቅነሳው ትግል ውስጥ የመንግሥትና የግሉ ዘርፍ አጋርነት ጎልብቶ የግሉ ዘርፍ ተሳትፎና አጋርነት ማደግ እንዳለበትም ምክራቸውን ገልገሰዋል፡፡

ለኢንዱስትሪ መሠረት የሆነ የግብርና ልማት፣ ዘመናዊ ቴክኖሎጂን በመጠቀም የግብርና ምርታማነትን ማሳደግ፣ የግብርና ምርታማነትንና የተፈጥሮ ሀብትን ከማስፋት ጎን ለጎን ዘርፈ ብዙ የአግሮ ፕሮሰሲንግ ምርቶችንና የማኑፋክቸሪንግ ኢንዱስትሪዎችን ማሳደግ፣ እንዲሁም ክልላዊና ዓለም አቀፋዊ ተወዳዳሪነትና ተፎካካሪነት ላይ የተመሠረተ የቀላልና ከባድ ኢንዱስትሪዎችን ማስፋፋት በሚሉት አራት መሠረታዊ ጉዳዮች ላይ በመመሥረት ኢትዮጵያ ወደ 21ኛው ክፍለ ዘመን የምታደርገውን ሽግግር እውነተኛና ውጤታማ ሽግግር ማድረግ ይቻላል ሲሉም ያላቸውን ምልከታ አስቀምጠዋል፡፡

የምክር ቤቱ ፕሬዚደንት ኢንጂነር መልአኩ በበኩላቸው ምሁራኑ ላቀረቡት አዲስ ሀሳብ በማመስገን እንደዚህ አይነት ጠቃሚ ሃሳቦች በተለይም የእርሻ፣ የከብት እርባታና ድለባ፣ የደን ልማት እና የመሳሰሉትን የሚያዘምኑ ፈጠራ ሀሳቦች የሚንሸራሸሩበት መድረክ መኖር አስፈላጊ ነው ብለዋል፡፡

ይህን ጠቃሚ ሀሳብ ለመተግበር ከፍተኛ ቁርጠኝነት የሚጠይቅ በመሆኑ በህዝቡ አስተሳሰብ ላይ አዎንታዊ ተፅዕኖ የማምጣት እና በተመረጡ ከተሞች ላይ የሙከራ ትግበራ ማሳየት እንደሚገባም ጨምረው ገልፀዋል፡፡

# ምክር ቤቱ የህንድ ልዑካን ቡድንን ተቀብሎ አነጋገረ

¶ 100 የህንድ ኩባንያዎች በ12ኛው ኢትዮ-ቻምበር ዓለም አቀፍ የንግድ ትርዒት ላይ ይሳተፋሉ



የኢንዶ-አፍሪካ ንግድና ኢንዱስትሪ ምክር ቤት ዋና ጸሐፊ ወ/ሮ ሱናንዳ ራጄንድራን 100 ያህል የህንድ ኩባንያዎች የኢትዮጵያ ንግድና የዘርፍ ማኅበራት ምክር ቤት በሚቀጥለው ዓመት በሚያካሂደው 12ኛው ኢትዮ-ቻምበር ዓለም አቀፍ የንግድ ትርዒት ላይ እናሳትፋለን አሉ፡፡

ዋና ጸሀፊዋ ይህን ያሉት የምክር ቤቱ ዋና ጸሐፊ አቶ እንዳልካቸው ስሜ ከም/ቤቱ ከፍተኛ ኃላፊዎች ጋር በመሆን በወ/ሮዋ የተመራውን የህንድ የንግድ ልዑካን ቡድን ነሀሴ 8 ቀን 2011 ዓ.ም. በምክር ቤቱ መሰብሰቢያ አዳራሽ ተቀብለው ባወያዩበት ወቅት ያደረጉላቸውን ግብዣ ተከትሎ ሲሆን የህንዶቹ ኩባንያዎች የውጭ ኩባንያዎችን ተሳትፎ በእጅጉ እንደሚጨምረው ይጠበቃል፡፡

በውይይታቸው ወቅት ዋና ጸሀፊዎቹ ምክር ቤቶቻቸው በሁለቱም ሀገሮች የንግዱ ማኅበረተሰብ መካከል አጋርነት መፍጠር በሚቻልበት ጉዳይ ላይ እንዴት መሥራት እንዳለባቸውም ውይይት አድርገዋል፡፡

ሁለት ቀናት ቀደም ብሎ ነሃሴ 6 ቀን 2011 ዓ.ም. የኢትዮጵያ-ህንድ ቢዝነስ ፎረም የተካሄደ ሲሆን ወደ ምክር ቤቱ ጉብኙት ያደረገው ልዑካን ቡድን አባላት በፎረሙ ላይ ከተካፈሉት የህንድ ኩባያዎች መካከል የአይ.ቲ. እና ፋርማሲውቲካል ኢንዱስትሪ ተወካዮች ናቸው፡፡

ፎረሙ በተካሄደበት ዕለት ኩባንያዎቹ በኢትዮጵያ የአይ.ቲ እና ፋርማሲውቲካል ኢንዱስትሪ ፓርኮችን መጎብኘታቸውን የገለጹት ወ/ሮ ሱናንዳ ኩባንያዎቹ ከኢትዮጵያ ኩባንያዎች ጋር በአጋርነት በመሥራት በዘርፎቹ መዋዕለ ንዋያቸውን ለማፍሰስ ፍላጎት እንዳላቸው ተናግረዋል፡፡

በዓለም አቀፍ የንግድ ትርዒቶች ላይ መሳተፍ ምርቶችን ከማስተዋወቅ ባሻገር ከሌሎች ሀገሮች ኩባንያዎች ልምድ ለመቅሰምና አጋርነትን ለመፍጠር ያስችላል ያሉት አቶ እንዳልካቸው የህንድ ኩባንያዎች በ12ኛው ኢትዮ-ቻምበር የንግድ ትርዒት ላይ የመሳተፋቸው አጋጣሚ ከሀገር ውስጥ ኩባንያዎች ጋር ይበልጥ ለመቀራረብ መልካም ዕድልን እንደሚፈጥርላቸው ገልጸዋል፡፡

አያይዘውም ንግድ ትርዒቱ ላይ ለአይ.ቲ እና ፋርማሲውቲካል ምርቶች የተሻለ ዕድልን መፍጠር እንደሚችሉ ያላቸውን ዕምነትም ገልጸውላቸዋል፡፡

የኢንዶ-አፍሪካ ንግድ ምክር ቤት ዋና ጸሐፊ ወ/ሮ ሱናንዳም በበኩላቸው በተመሳሳይ ዓመት በህንድ በሚካሄደው የፋርማ-ኤግዚቢሽን ላይ የኢትዮጵያ ኩባንያዎች እንዲገኙ ጋብዘዋል፡፡

## ፎረሙ የሁለቱን ሀገሮች . . .

(ከገጽ 4 የዞረ)

የህንድ ኩባንያዎች ከሀገር ውስጥ አቻዎቻቸው ጋር አጋርነት በመፍጠር መዋዕለ ንዋያቸውን በኢትዮጵያ እንዲያፈሱ ምክር ቤቱ ያበረታታልም ብለዋል፡፡

የኢንዶ-አፍሪካ ንግድና ኢንዱስትሪ ምክር ቤት ዋና ጸሐፊ ወ/ሮ ሱናንዳ ራጄንድራን ባደረጉት ንግግር የፎረሙ ዋና ዓላማ በኢትዮጵያና በህንድ መካከል ያለውን የሁለትዮሽ የንግድ ግንኙነት ይበልጥ ማሳደግና በሁለቱ ሀገራት የንግዱ ማኅበረሰብ መካከል የግንኙነት መደላድል በመፍጠር



የተሻለ የቢዝነስ ግንኙነት መፍጠር እንደሆነ ገልጸዋል፡፡

ፕሮጀክት ማኔጅመን ኮንሰልተንሲን፣ ቴክኖሎጂዎች፣ ጤና ጥበቃ፣ የወተትና ምግብ ውጤቶች፣ ትምህርት፣ ኤሌክትሮ ፕላስቲክ፣ አይቲ፣ በመሳሰሉት ዘርፎች ላይ የተሰማሩ 16 የህንድ ኩባንያዎች በፎረሙ ላይ መሳተፋቸው ታውቋል፡፡


ዋና አዘጋጅ፡- ደበበ አበበ

አዘጋጆች፡- ዮሴፍ ተሸመ

ጥበቡ ታዬ

ካሜራ፡- ያሬድ አባቡ

አድራሻ፡-

ስልክ-፡- +251-115-54-09-93

ፋክስ፡-+251-011-5517699

ድረ-ገጽ፡- www.ethiopianchamber.com